የሕክምና ውሳኔዎችዎን ማሳወቅ

# የመወሰን
# መብትዎ

INOVA® HEALTH SYSTEM

# የሕክምና ውሳኔዎችዎን ማሳወቅ

በ1990 ሕመምተኞች ለራሳቸው ውሳኔ ማድረግ የሚችሉበትን ሕግ (Patient Self-Determination Act) ኮንግሬስ አጸደቀ። የሕክምና ተቋሞች በቨርጂኒያ ሕግ መሠረት ለሕመምተኞቻቸውና ማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሰዎች ስለ ሕክምናቸው ውሳኔ መውሰድን በተመለከተ ያሏቸውን መብቶች እንዲያሳውቁ የሚያስገድድ ነው። እነዚህም መብቶች ሕክምና የመቀበል ወይም የመቃወም መብትንና ስለ ግል ሕክምና ቅድመ መምሪያ መስጠት የሚያስችሉም ናቸው።

ይህ መጽሔት ቅድመ መምሪያ መስጠትን በተመለከተ አዘውትሮ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ዓላማው ሕጋዊ ምክር ለመስጠት አይደለም።

ቅድመ መምሪያ መስጠትን በተመለከተ ይህ መጽሐፍ ያልመለሰው ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ተጨማሪ ውይይት ለማድረግ እና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ለማግኘት እባክዎን ኢኖቫ (Inova) ሆስፒታል ይደውሉና ማህበራዊ ሠራተኛ ለማነጋገር የጉዳይ አስተዳዳሪ ክፍል ስልክ ቁጥርን ወይም የሕመምተኛ ተወካይ ክፍልን ይጠይቁ።

የቅድመ መምሪያ ሰነድ ለማዘጋጀት ጠበቃ አያስፈልግዎትም፣ ሆኖም ጠበቃ ማማከር ከፈለጉ ባካባቢዎ የሚገኘው የጠበቃዎች ማሕበር ጋር ይደውሉ። የካውንቲዎ የጠበቃ ማሕበር ኢተርኔት ላይ ወይም የስልክ ቁጥር ማውጫዎ ውስጥ ማግኘት ይችላሉ።

ቅድመ መምሪያ ማለት የመረጧቸውን የሕክምና መንገዶች የሚገልጽ ሰነድ ነው። ዶክተሮች፣ የሕክምና አቅራቢዎች፣ ጠባቂዎች/አሳዳጊዎች፣ የሕክምና ውሳኔውችን ለማድረግ ውክልና የተሰጣቸው ሰዎች (Durable Power of Attorneys for Healthcare Decisions (DPOA))፣ ቤተሰቦች እና ሌሎች የሚመለከታቸው ሰዎች አቅም ላጡና ለማይችሉ አዋቂዎች ሕክምና ነክ ውሳኔ በሚወስዱበት ጊዜ ሰነዱ እንደ መምሪያ የሚያገለግል ነው። ሰነዱ ሶስት ክፍሎች አሉት፤ የሕይወት ኑዛዜ፣ የሕክምና ውሳኔዎች ውክልና (Durable Power of Attorney for Healthcare Decisions)ና ከሞቱ በኋላ የሰውነት ክፍሎችዎን፣ ቲሹዎችን ወይም ሰውነትዎን መመጽወት ከፈለጉ መምሪያ አለው። ስለ እያንዳንዱ መምሪያ ሰፋ ያለ መረጃ ቆየት ብሎ እዚህ መጽሔት ውስጥ ይገኛል።

ቅድመ መምሪያዎት ውስጥ ስለሚገኙት ነገሮች እባክዎ ከቤተሰብዎና ከሐኪሞችዎ ጋር ይወያዩ። ለራስዎ ውሳኔ ከመውሰድ የሚያግድዎት የመጨረሻ ደረጃ ሕመም ላይ ቢወድቁ፣ ሕክምናዎን በተመለከተ ምን ዓይነት ውሳኔ እንዲደረግ እንደሚፈልጉ በዚህ አጋጣሚ መወያየት ጥሩ ነው። ይህ ውሳኔ የተመሠረተው "ጥራት ያለው ሕይወት" ለእርስዎ ምን ማለት እንደሆነ በሚገልጹ ነገሮች ላይ ነው። እነሱ ለእርስዎ ስለ ሕክምናዎ የሚያደርጓቸው ውሳኔዎች የሕይወት ጥራትዎ ላይ ምን ዓይነት አጠቃላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው እንዲገነዘቡ ያድርጉ። ቅድመ መምሪያዎትዎን ከቤተሰብዎና ከዶክተሮችዎ ጋር ከተወያዩ በኋላ፣ የቅድመ መምሪያ ቅጽዎን (ቅጾችዎን) ግልባጭ ለዶክተሮችዎ በሙሉ የሕክምና ፋይሎችዎ ውስጥ እንዲከቱ ይስጧቸው። ስለ ሕክምና ባደረጉት ውሳኔ ዶክተርዎ የግብረገብ ወይም የሕክምና ተቃውሞ ቢኖረው ቅድመ መምሪያዎችዎን (Advance Directives) ያለመከተል ምርጫ አለው። ዶክተርዎ የሕክምና ውሳኔዎችዎን መከተል የማይችል/የማትችል ሆኖ ከተሰማው/ከተሰማት ውሳኔዎችዎን ማክበር ለሚሻ ለሌላ ዶክተር ፋይልዎን ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

**የሕክምና መብቶቼን እንዴት ነው የማስከብረው?**
በቨርጂኒያ ሕግ መሠረት "አዋቂ የሆነና አእምሮው ትክክለኛ የሆነ ሰው ሁሉ በራሱ ሰውነት ላይ ስለሚደርስ ሁሉ ውሳኔ የማድረግ መብት አለው።" ዶክተሮችም ሕመምተኞቻቸው ይህንኑ መብት እንዲያስከብሩ ስለሚያዙላቸው ሕክምናና ስለ አማራጮቻቸው መረጃ በመስጠት ይረዷቸዋል። ሕመምተኞች የታዘዘላቸውን ሕክምና እቀበላለሁ ሲሉ ስምምነታቸውን ሰጡ ማለት ነው። ሕመምተኞች የታዘዘላቸውን ሕክምና ያለመቀበልም መብት አላቸው።

**ቅድመ መምሪያው ውስጥ የሚገቡ ውሳኔዎች ምን ምን ዓይነት ናቸው?**
የቨርጂኒያ የሕክምና ውሳኔዎች ሕግ (Virginia Healthcare Decisions Act) የሕክምና ውሳኔዎችዎን በሶስት የተለያዩ መንገዶች እንዲያደርጉ ይፈቅድልዎታል፤

1. የመጨረሻ ደርጃ ላይ ያለ ሕመም ከያዝዎትና ስለ ሕክምናዎ ውሳኔ የማድረግ አቅም ካጡ ምን ዓይነት እርምጃዎች እንዲወሰዱ እንደሚፈልጉ የሚተነትን "የሕይወት ኑዛዜ" ("living will") መጻፍ ይችላሉ።
2. እራስዎ ውሳኔ የማድረግ አቅም በሚያጡበት ጊዜ በቦታዎ ሆኖ በሕጋዊ መንገድ የሕክምና ውሳኔ እንዲያስተላልፍልዎት ለአንድ ሰው ውክልና (Power of Attorney for Healthcare Decisions (DPOA)) መስጠት ይችላሉ - የሕመምዎ ደረጃ አይወስነውም። የሕክምና ውክልና የተሰጠው ሰው (DPOA) እነዚህን መምሪያዎች ለመከተል የግድ ሕመምዎ የመጨረሻ ደረጃ ላይ መድረስ የለበትም።
3. ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ የሰውነት ክፍሎችዎ፣ ቲሹዎችዎና ሰውነትዎ ምን እንደሚደረግ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ።

እነዚህ የቅድመ መምሪያ ክፍሎች በሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል።

**የሕይወት ኑዛዜ ምንድን ነው?**
የመጨረሻ ደረጃ ሕመም ላይ ከሆኑና ለራስዎ ውሳኔ የማድረግ አቅም ከሌልዎት እንዴት መታከም እንደሚፈልጉ የሕይወት ኑዛዜ ይገልጻል። ይህ ሰነድ "የሕይወት ኑዛዜ" ("living will") ይባላል። የመጨረሻ ደረጃ ሕመም ማለት የማይድን ደረጃ ላይ ያለ በሽታና ቢቆይ በስድስት ወር ውስጥ ለሞት የሚዳርግ ሁኔታ ነው። "የመጨረሻ" ማለት ለሞት ወዲያው የሚዳርግ ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ሕሊናን መሳት ወይም ኮማ ውስጥ መሆንም ሊሆን ይችላል። ባጠቃላይ፣ የመዳን ተስፋ እንደሌለ ሐኪም የወሰነበት ሁኔታ ነው ማለት ነው።

ይህን ዓይነት ቅድመ መምሪያ ፈርሞ ማስቀመጥ ሕጉ "የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎች" ("life-prolonging procedures") የሚባሉትን ሕክምናዎች ዶክተሮችዎ እንዲሰጡዎት መፈለግዎንና አለመፈለግዎን በቅድሚያ መወሰን እንዲችሉ ይጠቅማል። ልብ ይበሉ፣ የሕይወት ኑዛዜ በሥራ ላይ የሚውለው እርስዎ ውሳኔ የማድረግ አቅም ካጡ ብቻ ነው። አለበለዚያ ሐኪምዎ እነዚህን ውሳኔዎች በቀጥታ ከራስዎ ጋር ይወያያል/ትወያያለች።

**"የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎች" ምንድን ናቸው?**
እነዚህ ሕክምናዎች የመጨረሻ ደረጃ ላይ ያለ በሽታን እንዲያድኑ ወይም እንዲሻልዎት የሚደረጉ አይደሉም። ሞትን የሚያዘገዩ ብቻ ናቸው። ሕክምናዎቹ ሃይድሬሽን (ውሃ መስጠት)፣ የቱቦ ንዩትሪሽን (ምግብ መስጠት)፣ ለመተንፈስ የሚረዱዎት ማሽኖች ጋር ማገናኘትና እንደ ኩላሊት ማጣሪያ የመሳሰሉ የሕክምናና የቀዶ ጥገና ሕክምናዎች የመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎች ሕመምዎን የሚቀንሱና በይበልጥ ምቾት እንዲኖርዎት የሚያደርጉ ሕክምናዎችን ሊያካትቱም፡ ቅድመ መምሪያዎ ውስጥ አልፈልግም ካላሉ በስተቀር ሐኪምዎ ሁልጊዜም ቢሆን ሕመምዎን የሚያስታግስና ምቾትዎን የሚጨምር ሕክምና ወይም መድኃኒት የሰጥዎታል። እንደዚህ ዓይነት ቅድመ መምሪያ ውስጥ የተወሰኑ ዓይነቶች የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎች እንደሚፈልጉም መጥቀስ ይችላሉ። ለምሳሌ የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎች በሙሉ እንዲደረግልዎት ሆኖም የቱቦ አመጋገብ እንዲቀርብዎት ከፈለጉ ይህንኑ ቅድመ መምሪያዎ ውስጥ መግለጽ ይችላሉ።

የሕክምና ሁኔታዎ እየገፋ ሲሄድ እርስዎ ወይም የሕክምና ውክልና የሰጡት ሰው (DPOA) ተከታታይ ውሳኔዎች እንድታደርጉ ልትጠየቁ ትችላላችሁ። ይህ የሚያሳየው መምሪያዎን የመከተል ግዴታ ያለበት ውክልና የሰጡት ሰው (DPOA) ጋር የሕክምና ፍላጎትዎን በግልጽ መወያየትዎ ምን ዓይነት አስፈላጊነት እንዳለው ነው። ሕመምዎ እየገፋ በሚሄድበት ጊዜ ምን ዓይነት አማራጮች እንዳሉዎት ዶክተርዎ ከእርስዎ ወይም ከተወካይዎ ጋር ይወያያል። ይህም "የሕይወት ማራዘሚያ" ሕክምናዎችና ሂደቶችን የማቆም ውሳኔዎችን ሊያካትት ይችላል። እንደ ማንኛውም የሕክምና ውሳኔዎች፣ እነዚህን ሕክምናዎች በማንኛውም ወቅት የመቃወም መብት በሕግ አልዎት።

**በሕክምና ውሳኔዎች ሕግ (Healthcare Decisions Act) መሠረት የሕይወት ማራዘሚያ ሕክምናዎችን አልፈልግም ብዬ ብሞት የእራሴን ሕይወት እንዳጠፋሁ ይቆጠርብኛል?**
አይ። የሕክምና ውሳኔዎች ሕግ (Healthcare Decisions Act) በተለይ እንደሚለው በሕክምና ላይ ሆኖ ሕመምተኛው ቢያርፍ፣ ራሱን እንደመግደል አይታይም። በሕጉ መሠረት መሄድም የሕይወት ዋስትናን አይሽርም፣ ዋስትናው ሌላ ቢልም።

**የሕክምና ጉዳዮች ውሳኔዎችን አስመልክቶ ቋሚ ውክልና (Durable Power of Attorney for Healthcare Decisions) የተሰጠው ማለት ምን ማለት ነው?**

የሕክምና ጉዳዮች ውሳኔቸውን አስመልክቶ ቋሚ ውክልና (Durable Power of Attorney for Healthcare Decisions (DPOA)) ማለት በቅድመ መምሪያ ውስጥ ያለው ሁለተኛው ዓይነት ውሳኔ ነው። ተወካዩ (DPOA) በአካል ወይም በአእምሮ ሕመም ምክንያት ውሳኔ ማድረግ ቢያቅቶት እንደ እርስዎ ሆኖ ውሳኔ እንዲያስተላልፍልዎት የመረጡት ሰው ነው። የቅድመ መምሪያው (Advance Directive) ቅጽ (እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ) የተወካዩን (DPOA) ሥልጣኖች ይገልጻል። ተወካይዎ (DPOA) እንዲኖረው/እንዲኖራት የማይፈልጉትን ሥልጣኖች መሰረዝ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ቅድመ መምሪያ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰው ሰው የማይድን በሽታ ቢይዝዎትም ባይዝዎትም ለእራስዎ ውሳኔ እንደሚያድርጉ ሆኖ የሕክምና ውሳኔ በሙሉ በእርስዎ ፋንታ የሚያደርግልዎት ሰው ነው። ይህ ሰው ሃይማኖትዎንና ዋጋ የሚሰጡትን ነገር ወይም የገለጹትን ፍላጎት የሚጻረሩ ውሳኔዎች ማስተላለፍ እንደማይችል የቨርጂኒያ ሕግ ይገልጻል።

**ከሞትኩ በኋላ የሰውነት ክፍሎቼን፣ ቲሹዎቼን ወይም ሰውነቴን ስለ መመጽወት ያደረኩትን ውሳኔዎች እንዴት ነው የማሳውቀው?**

ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ የሰውነት ክፍሎችዎ፣ ቲሹዎችዎ ወይም ሰውነትዎ እንደሚመጸወቱ የሚያረጋግጥልዎት ሰው በስም እንዲመድቡ ሶስተኛው መምሪያ ይፈቅድልዎታል። ስለ እንደነዚህ ዓይነት ምጽዋቶች ጥያቄዎች ካልዎት የዋሽንግተን አካባቢ የትራንስፕላንት ማሕበረሰብ (Washington Regional Transplant Community) ጋር በስልክ ቁጥር 703-641-0100 ይደውሉ። በሕጉ መሠረት፣ ውክልና የሰጡት ሰው (DPOA) ስለነዚህ መጽዋቶች የሰጡትን መምሪያ መከተል አለበት።

**በድንገተኛ ጊዜ ፍላጎቴን ማሳወቅ ካልቻልኩ ቅድመ መምሪያዬን ይከተላሉ?**

ከአደጋ አዳኝ ቡድኖች ወይም የአንቡላንስ ሠራተኞችን የመሳሰሉ የድንገተኛ ሕክምና ሠራተኞች በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ተጠርተው ሊረዱዎት ሲመጡ የቅድመ መምሪያዎ ውስጥ ያሉትን ፍላጎቶችዎን መከተከል በሕግ አይፈቀድላቸውም። እንዲሁም የሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በድንገተኛ ጊዜ ፍላጎቶችዎን ላያውቁ ይችላሉ። ሆኖም የማይድንና መጨረሻ ደረጃ ላይ ያለ ሕመም ካለብዎት አንዳንድ ጊዜ የተወሰነ ዓይነት የድንገተኛ ሕክምና በቅድሚያ የመቃወም መብት አልዎት - ለምሳሌ ልብዎ መምታት ቢያቆም ወይም መተንፈስ ቢያቆሙ መልሶ ነፍስ የመዝራት/የመቀስቀስ ሕክምና። ይህንን የሚያደርጉት ስቴቱ ባጸደቀው ቅጽ ላይ ሐኪምዎ "መልሶ እንዳይቀሰቀስ ቋሚ ትእዛዝ" ("Durable Do Not Resuscitate Order") (ብዙ ጊዜ "ቋሚ የDNR ትእዛዝ" ተብሎ የሚታወቅ) እንዲሞላልዎት በማድረግ ነው። በተጨማሪም በሆስፒታል ውስጥ ወይም ነርሲንግ ሆም/ቋሚ የእንክብካቤ ተቋም ውስጥ ተግባር ላይ የሚውል ለመቀስቀስ አይሞከሩ/የተፈጥሮ አሟሟት ፈቃድ (Do Not Attempt Resuscitation/Allow a Natural Death (DNAR/AND)) ትእዛዝ ዶክተርዎ ሊጽፍልዎ ይችላል። እርስዎ ካልሰረዙት በስተቀር ትእዛዙ ተግባር ላይ ይውላል፣ ማለትም ውሳኔ የማስተላለፍ አቅም ሲኖርዎት ሐሳብዎን ቀይረው መቀስቀስ እንደሚፈልጉ ለዶክተርዎ ሲነግሩት።

**ቅድመ መምሪያ በጽሑፍ መቅረብ አለበት?**

የለበትም ግን ይህ የሚሆንበት ልዩ ሁኔታዎች አሉ። የሕክምና ውሳኔዎች ሕግ (Healthcare Decisions Act) የመጨረሻ ደረጃ ላይ ያለ በሽታ ያለባቸውና ቅድመ መምሪያ ያልፈረሙ ሕመምተኞች በቃል ቅድመ መምሪያ እንዲሰጡ ይፈቅዳል። በዶክተራቸውና በሁለት ምስክሮች ፊት ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ መንገር ወይም በእነሱ ቦታ ሆኖ ውሳኔ የሚያስተላልፍላቸው ሰው በስም መመደብ ይችላሉ። ዶክተሩም በቃል የተሰጠውን ቅድመ መምሪያ የሕክምና ፋይል ውስጥ ይመዘግብና ምስክሮቹን ይጽፋል።

**ቅድመ መምሪያ ያስፈልገኛል?**

አያስፈልግዎትም። ቅድመ መምሪያ በተለይ እርስዎ የመንገር አቅም ቢያጡ ዶክተሮችዎና የሚወዷቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሕክምና እንደሚፈልጉ እንዲያውቁ የሚያደርጉበት አንዱ መንገድ ነው። አንድ፣ ሁለት ወይም ሶስቱም ዓይነት ቅድመ መምሪያ እንዲኖርዎት ማድረግ ይችላሉ። የሕክምና ሰጪዎች ቅድመ መምሪያ ባላቸውን በሌላቸው ሰዎች መካከል አድሎ እንዳያደርጉ ሕጉ ይከለክላል።

**ውሳኔ የማድረግ አቅም ከሌለኝና ቅድመ መምሪያ ከሌለኝ ምን ይሆናል?**
ቅድመ መምሪያ ባይኖርዎትም የቨርጂኒያ ሕግ እንደ ጠባቂና የቤተሰብ አባሎች የመሳሰሉ ሰዎች ስለ ሕክምናዎ ውሳኔ ማድረግ የሚችሉ ብሎ ዘርዝሯቸዋል። በቨርጂኒያ ውስጥ የውሳኔ ሰጪ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው፤ በመጀመሪያ ሕጋዊ መጉዚት/አሳዳጊ፣ ቀጥሎ በሕክምና ጉዳይ ውክልና የተሰጠው ሰው (DPOA for Healthcare Decisions)፣ ባለቤት፣ ልጆች በመጨረሻም ሌሎች ዘመዶች። ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱም ባይገኝ ዳኛ የትኛው ሕክምና እንደሚሻል ይወስናል። የሕይወት ጓደኛ ወይም ባልንጀሮች በቅድመ መምሪያ ውስጥ ለሕክምና ውክልና ካልተሰጣቸው በስተቀር ውሳኔ መስጠት አይችሉም።

**ቅድመ መምሪያ ለማውጣት ጠበቃ ያስፈልገኛል?**
አያስፈልግዎትም። ጠበቃ ሊረዳ ይችላል ግን ማንኛውንም ዓይነት ቅድመ መምሪያ ለማዘጋጀት ጠበቃ አያስፈልግዎትም። እንዲያውም የሕክምና ውሳኔዎች ሕግ (Healthcare Decisions Act) ሊጠቀሙት የሚችሉት ቅጽ አዘጋጅቶ እዚህ መጽሔት ውስጥ ይገኛል። ሰነዱ ሕጋዊ ማህተም ባያስፈልገውም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሁለት ምስክሮች ፊርማ ያስፈልገዋል። ምስክሮቹ በፊርማቸው የሚያረጋግጡት ሰነዱን እርስዎ እንደፈረሙ ነው እንጂ ይዘታው ሥራ ላይ እንደሚውል አይደለም። ግጭት እንዳይፈጠር ውክልና የሰጡት ሰው (DPOA) ከምስክሮችዎ አንዱ ባይሆን ይመረጣል።

**ቅድመ መምሪያውን ከፈረምኩ በኋላ ሐሳቤን ብቀይርስ?**
መሰረዝ ይችላሉ። ከፈለጉ አዲስ መጻፍ ይችላሉ። የሕክምና ተቋም ውስጥ ያሉ ሕመምተኛ ወይም ኗሪ ከሆኑ ቅድመ መምሪያዎትን መሰረዝ ወይም መቀየር እንደሚፈልጉ ዶክተርዎን ወይም ነርስዎን ይንገሯቸው። በችግር ጊዜ የሕክምና ውሳኔዎችዎንና ማን እንደሚወስን በተመለከተ አለመግባባት እንዳይፈጠር የድሮውን መምሪያ ግልባጮች ሁሉ ማስወገድ ጥሩ ነው።

**ዶክተሬ (ሮቼ) ቅድመ መምሪያ እንዳለኝ በምን ያውቃል (ሉ)?**
በሚቀበሉዎት ጊዜ፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች የሕክምና ተቋሞች ሕመምተኞችንና ኗሪዎችን ቅድመ መምሪያ እንዳላቸ መጠየቅና ካላቸው የመምሪያውን ግልባጭ የሕመምተኛው ወይም የኗሪው ፋይል ውስጥ እንዲከቱ መጠየቅ አለባቸው። ለማንኛውም የቅድመ መምሪያ ግልባጮች ለቤተሰብዎ እና ለዶክተርዎ እንዲሁም ሌላ ስለሚፈልጉት ሕክምና ማወቅ አለበት ለሚሉት ሰው መስጠት አለብዎት። ያስታውሱ፣ ቅድመ መምሪያዎን ከቀየሩ የአዲሱን መምሪያ ግልባጭ ለእያንዳንዱ ሰው መስጠት እንዳይረሱ።

Notice to Health Care Providers/ለሕክምና ሰጪዎች ማሳሰቢያ፤

I, _______________________________________________, have executed an advance medical directive and have given a copy of such document to:

እኔ ______________________________________________ የሕክምና ቅድመ መምሪያ ጽፌ ግልባጩን ለሚከተሉት ሰዎች ሰጥቻለሁ፤

_______________________________________________________________

Name (ስም) Phone (ስልክ)

_______________________________________________________________

Address (አድራሻ)

_______________________________________________________________

Name (ስም) Phone (ስልክ)

_______________________________________________________________

Address (አድራሻ)

Signed (ፊርማ)_______________________________________________

Date (ቀን)__________________________________________________

የቨርጂኒያ ጤና መምሪያ (Virginia Department of Health) እና የቨርጂኒያ አዛውንቶች መምሪያ (Virginia Department for the Aging) ይህ መጽሔት እንዲታደል በፌዴራል ሕጉ ትእዛዝ መሠረት አጽድቀዋል።
*(ዳግም የታየው 7/98፣ ወቅታዊ 3/06፣ ዳግም የታየው IHS 3/08)*